# ኅዳር ሲታጠን

በሲሳይ ጌቴ

የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ማብቃቱ ሊታወጅ ጥቂት ሲቀረውና ዕልቂቱ ቆመ ሲባል የዓለም ህዝብ ሌላ ፍዳ ማስተናገድ ግድ ሆነበት፡፡ በሰው ሰራሽ ችግሮች (በተለይም በጦርነት) ተወጥሮ የቆየው መላው የአለም ህዝብ አሁን ደግሞ በኢንፍሉዊንዛ በሽታ ከዳር እስከ ዳር ተጠቃ፡፡ በተለምዶ “ስፓኒሽ ፍሉ” ተብሎ የሚታወቀው ይህ ወረርሽኝ መነሻው ከወደ አሜሪካ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም እ.ኤ.አ በጥር ወር 1918 ዓ.ም በአንደኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ ዋዜማ በጦርነቱ ለመካፈል የአሜሪካ ወታደሮች ወደ አውሮፓ ለመንዝ ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት ነበር፡፡

በካንሳስ በሚገኘው ፉንስተን የወታደራዊ ማሰልጠኛ ማዕከል የተቀሰቀሰው ወረርሽኙ በሶስት ቀናት ብቻ 45 ሺህ የሚሆኑ ወታደሮችን አጠቃ፡፡ ወታደሮቹ አትላንቲክን አቋርጠው አውሮፓን እንደረገጡ በሽታውም አውሮፓ ደረሰ፡፡ የኢንፍሉዌንዛ በሽታ በአውሮፓ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው በፈረንሳይ ቢሆንም በጦርነቱ ምክንያት ፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ይሆናል በሚል ወረርሽኙ ለህዝብ ሳይገለጽ ተደብቆ ቆይቷል፡፡

በሽታው ለአለም ይፋ የሆነው እ.ኤ.አ በህዳር ወር 1918 ዓ.ም በስፔን ለመጀመሪያ ጊዜ መታየቱን ተከትሎ ነበር፡፡ ስፔን በጦርነቱ ተካፋይ አልነበረችምና በአገሪቱ የጦርነት ጊዜ ቁጥጥር አልነበረም፡፡ በመሆኑም የበሽታው መስፋፋት ከፍተኛ የሆነ የሚዲያ ሽፋን በማግኘቱ ወረርኙ ስፓኒሽ ኢንፍሉዌንዛ (ስፓኒሽ ፍሉ) የሚለውን ስያሜ አገኘ፡፡

የበሽታው ምልክቶች ሳል፣ ከፍተኛ ትኩሳት፣ ነስር፣ የጆሮና የአንጀት መድማት፣ ተቅማጥ፣ የአይን ማስለቀስ፣ ውጋት እንዲሁም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ የአእምሮ ህመም ያስከትላል፡፡ በዚህም በሽታው ከኮሌራ ወይም ከፈንጣጣ በሽታዎች ጋር ተተቀራራቢ ምልክቶችን

ስለሚያሳይ ብዙ ያምታታ ነበር። የበሽታው አስገራሚ ባህሪ አንድ ሰው በበሽታው በተጠቃ በአምስት ቀን ውስጥ ይሞታል አልያም ከበሽታው ሙሉ ለሙሉ ይፈወሳል።

በጥቂት ጊዜም ከአሜሪካ እስከ አውሮፓ፣ ከኤሺያ እስከ አፍሪካ፣ከአርክቲክ እስከ ፓስፊክ ደሴቶች ድረስ በከፍተኛ ፍጥነት ተዛመተ። በሽታው እንዲዛመት የአለም የወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮ ነበር፤፡ ይህም ወታደሮች ከአንዱ የአለም ክፍል ወደሌላው ለዘመቻ መንቀሳቀሳቸው ነበር። በዚህም አንድ ሶስተኛው የአለም ህዝብ በዚህ በሽታ እንደተያዘ ይነገራል። በበሽታው ከተያዙት ውስጥ ደግሞ ከ 10 እስከ 20 በመቶ የሚሆት ለሞት ተዳርገዋል።

ይህን አስመልክቶ ሲኖ ባይሎጂካ የተሰኛ የህክምና ጥናት ማዕከል ባደረገው ጥናት መሰረት እ.ኤ.አ ከጥር ወር 1918 ዓ.ም እስከ ታህሰስ 1920 ዓ.ም በመላው ዓለም ተንሰራፍቶ የቆየው የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ የማቾቹ ቁጥር እስከ 200 ሚሊዮን እንደሚሆን ይገልፃል። በበሽታው ከሞቱት መካከል ዕድሜያቸው ከ 25 እስከ 34 ዓመት የሆኑ ወጣቶች አብዛኛውን ድርሻ ይወስዳሉ። በመሆኑም በሽታው ካደረሰው ሰብዓዊ ውድመት ባለፈ ጥሎት ያለፈው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠባሳ የከፋ ነበር።

በሽታው ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ የታየው በወቅቱ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችው በሴራሊዮን ዋና ከተማ ፍሪታዎን ሲሆን በአጭር ጊዜ ወደሌሎች የአፍሪካ አገራት ተስፋፋ። የበሽታው ስርጭት ከሰሃራ በታች በሚገኙ አገራት ላይ ሰፊ ነበር። በክፍለ አህጉሩ የተከሰተው የሞት መጠን በመላው ዓለም በበሽታው ከተከሰተው ሞት ውስጥ የ 29 በመቶ ድርሻ አለው።

በሽታው ዘር፣ ቀለም፣ ሀይማኖት፣ የኢኮኖሚ ደረጃን ሳይለይ ሁሉንም ሰው የሚያጠቃ ቢሆንም ቅኝ ገዢዎች በሽታው ከጥቁር ህዝቦች የመጣ እንደሆነ በማናፈስ የዘር መድሎ በማድረግ ተጠቅመውበታል። ይህ ችግር በተለይም በደቡብ አፍሪካ የጎላ ነበር። በዚህም

ነጮችና ጥቁሮች ማንኛውንም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በአንድ ላይ እንዳያደርጉ የሚደነግግ አዋጅ እንዲጸድቅ ተደረገ፡፡

በኢትዮጵያ በሽታው የታየው የመጀመሪያው የበሽታው ምልክት በዓለም ላይ ከታየ ከአስር ወር በኋላ በኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር በህዳር ወር 1911 ዓ.ም ነው፡፡ ወረርሽኙ ከዘመናዊ የህክምና ጋር ለማይተዋወቀው የኢትዮጵያ ህዝብም ታላቅ መቅሰፍት ነበር፡፡ በሽታው ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ በመላው አገሪቱ ከባድ ዕልቂት ማስከተል ጀመረ፡፡ በተለይም ታላላቅ ኢትዮጵያዊያን በበሽታው መያዛቸውን ተከትሎ መረበሽን ፈጥሮ ነበር፡፡ በበሽታው ከተጠቁ ታላላቅ የዘመኑ ሹመኞችና የቤተ መንግስት ሰዎች መካከል ራስ ተፈሪ መኮንን (ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ) እና ባለቤታቸው ወ/ሮ እቴጌ መነን አስፋው እንደሚገኙበት የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡

በኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር ከህዳር 7 እስከ ህዳር 20 1911 ዓ.ም ለአስራ አራት ቀናት ገደማ የቆየው በሽታው በህዳር ወር የተከሰተ በመሆኑም ህዝቡ የህዳር በሽታ እያለ ይጠራው ጀመር፡፡ ብላቴን ጌታ መርስዔ ሀዘን ወልደቂርቆስ “የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ” በተሰኘው መጽሀፋቸው እንዳሰፈሩት ወረርሽኙ እስከ 40 ሺህ ኢትዮጵያዊንን ለሞት ዳርጓል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ዘጠኝ ሺህ ዜጎች በበሽታው ሞተዋል፡፡ በተለይም ህዳር 12 ቀን 1911 ዓ.ም በርካታ ኢትዮጵያዊያን የሞቱበት በመሆኑ ቀኑ በጽዳት ዘመቻ እንዲደረግ በአዋጅ ተነግሮ ስለነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር እንደባህል ተወስዶ በየዓመቱ ህዳር 12 ቀን የጽዳት ዘመቻ ይደረግ ጀመር፡፡ ይህም በተለምዶ ህዳር ሲታጠን የሚል መጠሪያን እንዲያገኝ ሆኗል፡፡